# በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ስማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2001

በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈያ ጊዜን በግልጽ ማስቀመጡ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 35 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   "አዋጅ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 ነው።

3. **የኤክሳይዝ ታክስ መክፈያ ጊዜ**

   1. በአዋጁ አንቀጽ 6(2) (ሀ) (2) መሠረት ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች በአገር ውስጥ ሲመረቱ ከተመረቱበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል።
   2. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም በዕቃዎቹ ላይ ታክሱ የሚከፈለበት ጊዜ ዕቃዎቹ ከተመረቱበት ወር ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ነው።

4. **የተሻሩ መመሪያዎች**

   ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የነበሩ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።

5. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ 29/12 ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር